# ዴሞክራሲያ

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *


## በሽግግር ሂደት እንታደግ !


ዴሞ ቅጽ 45 ቁ. 1 ነሐሴ 2011 - መስከረም 2012


ኢትዮጵያዊነት የረጅም ዘመን ባለታሪክነት፥ የጀግንነት፥ የልበሙሉነት፣ አብሮ የመኖርና የነፃነት ፣ ...ወዘተ መገለጫ ሲሆን ከሁሉም በላይ ደግሞ ኢትዮጵያዊነት ለሀገር ታዳጊነት፣ ለወገን ተቆርቋሪነት፣ ለፍትህ መቆም፤ ለነፃነት መስዋዕት መሆን ፣ ባህላዊና ቁሳዊ ቅርስን ማቆየት ማለት ጭምር ነው። ይህ ማንነትም ነው በዓለም ታሪክ ኢትዮጵያዊነት የነፃነት ቀንዲልና የአይበገሬነት መገለጫ ሆኖ እንዲታይ ያደረገው።

ኢትዮጵያዊያን የሚታወቁት ሉዓላዊነታቸውን ለመድፈር ፤ ነፃነታቸውንና ክብራቸውን ለመግፈፍ፤ በቃጡ የውጭ ወራሪዎች ላይ ብቻ ሳይሆን በአገራቸው የአገዛዝ ሥርዓቶች ላይም ጭቆናና በደልን፥ ግፍንና ኢ-ፍትሃዊነትን ፀንተው በመታገላቸው ጭምር ነው። ከላይ የገለጽነው ኢትዮጵያዊ ወኔና የትግል ስሜት ከጀግኖች እናቶችና አባቶች በመተላለፉ የሀገርና የወገንን ፍቅር የተረዱ ለውጥ ፈላጊ የሆኑ የዘመኑ ወጣት አርበኞች የሚወዷትን እናት አገራቸውን ኢትዮጵያን ከውጭ ወራሪዎች ለመታደግ በዱር በገደሉ በመዋደቅ አጥንታቸውን ከስክሰው፤ ደማቸውንም አፍሰሰው ፤ አርበኝነታቸውን አስመስክረው፤ ሉዓላዊት የሆነች አገር ለትውልድ አሸጋግረዋል።

የፋሽስት ጣሊያን ወረራ ካከተመ ከ1933 ዓ.ም በኋላ የነበረው በተለይም ዘመናዊ ትምህርትን ለመቅሰም እድል ያገኘው አገርወዳድ ወጣት ትውልድ፤ ለፍትህ ከነበረው የጠለቀ ግንዛቤና ፍላጎት የተነሳ የአገሩና የወገኑ ችግርና ብሶት እጅግ ያሳሰበውና በአፍላ ወጣትነት ዘመኑ ዘላቂ መፍትኄ ለመሻት የተለያየ ትግልን በመጠቀም እንቅስቃሴ ሲያደርግ የነበረ ፍትኀን ናፋቂ ትውልድ ነበር። የ1950ዎቹ የእነ ገርማሜና ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ፤ የኤርትራ ነፃ አውጭ ግንባር መቋቋም፤ የሜጫና ቱለማ እንቅስቃሴ፣ በጎጃም የነበረው የገበሬዎች አመጽ የወቅቱን የሕዝብ ብሶት በተለያየ መልክ የሚያሳዩ ነበሩ። በአርሶ አደሩ ላይ የተጫነው የመሬት ግብር አለመጠን መጨመር ፤ ግብሩን መክፈል የተሳነው አርሶ አደር መሬቱን መነጠቁና፤ በ1955 ዓ.ም በተካሄደ የመሬት መለካት አዲስ ሕግ መውጣቱ እየተብላላና እየተቀጣጠለ ለሚሄደው ብሶት ተጨማሪ ምክንያቶች ነበሩ። የጎጃም፣ የባሌና የሲዳሞ አርሶ አደሮች አመፅን ለመግታት በወቅቱ የተወሰደው ወታደራዊ የኃይል እርምጃ የሕዝቡ ትግል ይበልጥ እንዲቀጣጠል ምክንያት መሆኑ አልቀረም። የሥርዓቱ አገልጋይና ጠባቂ ሆኖ የተደራጀው ወታደርም ህይወቱ ከጊዜ ወደጊዜ እየከፋና እየመረረ ሄደ። በወቅቱ በመላው ሀገሪቱ ውስጥ ይታይ የነበረው ግፍና በደል ከልክ በላይ መግዘፍ፤ (የፍትህ መራቆት) በላብ-አደሮችና በተማሪዎች ተቃውሞ ከፍተኛ የውጥረት ዘመን ሆነው መደምደማቸው ሀገሪቱ የአዲስ ሥርዓት/የለውጥ ፅንስ መቋጠሯን ያበሰረበት ሁኔታ እንደነበረ መገንዘብ ይቻላል ።

በወቅቱ ተደራጅተው ይካሄዱ ከነበሩት የትጥቅ ትግልና የአርሶአደሮች አመጽ እንቅስቃሴዎች ሌላ ከ1950ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ በከተማም የሲቪል እንቅስቃሴዎች ተጠናክረው ነበር። በእነዚህ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተሳታፊዎች የነበሩት ያነሱዋቸው ጥያቄዎች ባብዛኛው ያጠነጥኑ የነበሩት በመብትና በኑሮ ወድነት ላይ ያተኮሩ ነበሩ። የአየር መንገድ አድማ በ1959 እና በ1960ዓ.ም የተደረገው የአውቶቡስ ሾፌሮችና የማተሚያ ቤት ሠራተኞች አድማ ፤ እንዲሁም በ1965ዓ.ም የተካሄደውን የባንክ ሠራተኛችን አድማ ለአብነት መጥቀስ ይቻላል።

ከታኅሣሡ መፈንቅለ መንግሥት እንቅስቃሴ በኋላ የተከተለው የ1960ዎቹ ወጣት ትውልድ ለኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት ተጠብቆ መቆየት ቀናኢ ፤ ፍትህ ናፋቂ ፤ አምባገነን ገዥዎችን ተቃዋሚና ተሟጋች እንዲሁም ለውጥ ፈላጊ ለመሆኑ የትግል ታሪኩና ተግባሩ ምስክር ናቸው። የዚያ ትውልድ የተማረ ክፍል የኢትዮጵያን ሁኔታ እንዴት መለወጥ እንደሚቻል በአንክሮ መጠየቅ የጀመረ ፤ የሀገሩን የቅርብና የሩቅ ሁኔታዎች ለመረዳት የአካባቢውንና የአፍሪካን ሰፋ አድርጎም የዓለም አቀፉን ተጨባጭ ሁኔታ ለማየት የሞከረ መሠረታዊ የሰው ልጅ መብቶችንና ፍላጎቶችን በውል የተረዳ

ትውልድ ነበር። ያ ትውልድ እድሜውና እውቀቱ በፈቀደለት ደረጃ ከመመራመር አልፎም እውቀትና አቅሙ የፈቀደለትን ሁሉ ለማገናዘብ ተገቢውንም ትምህርት ለመቅሰምና በአግባቡም ለመፍታት ይቻላል የሚል ተስማሚ ንድፈ-ሐሳባዊ መመሪያ ለማግኘትና የሚወዳት አገሩን ወደተሻል ደረጃ ለማድረስ ቅን በሆነ አዕምሮ የሚችለውን ሁሉ ለማድረግ ከልቡ ጥሯል። ለሀገሩና ለሚወደው ሕዝብ ሲልም መከፈል የሚገባውን የህይወት መስዋዕትነትም ከፍሏል።

ያ አገር ወዳድ ትውልድ አገሪቱን ለውጭ ባለሀብቶችና ጎጅ ተልዕኮ ለነበራቸው ባዕዳን (ሚሲዮናውያን/ሚሽነሪዎች) በሯን በርግዶ ሕዝቧን ለብዝበዛ፣ ደህንነቷን ለአደጋ ያጋለጠ ኋላቀር ሥርዓትንና እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃም ተስፋፍቶ የሰው ልጆች እኩልነትንና መሠረታዊ የሰብዓዊ መብትን በመጻረር ብዝበዛ ያካሂድ የነበረውን የቅኝ አገዛዝ (አፓርታይድን) አጥብቆ ሲቃወምና ሲታገልም የነበረ ብርቅዬ ትውልድ ነበር ።

በወቅቱ በመላ ሀገሪቷ የተዛባ ፍትኀ፣ ዝቅተኛ የትምህርትና የጤና አገልግሎት፣ የተስፋፋ የሥራ አጥነት፤ ... መስፈናቸውን ተገንዝቦ የዜጎችን መብትና ጥቅም ለማስከበርና በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አገራዊ አንድነትን ለማጠንከር፤ ማኅበራዊ ፍትህን ለማስገኘት፤ ፈጣን ኢኮኖሚያዊና የቴክኖሎጂ እድገት ለማምጣት ትልቅ ሀገራዊ ራዕይ አንግቦ ብሩህ ተስፋን ሰንቆ ተሰባስቧል፣ ተደራጅቷል ለትግልም ተሰልፏል። ይህ ለወጥ ፈላጊ የኅብረተሰብ ክፍል ነው እነዚህን ከላይ የጠቀስናቸውንና ሌሎችንም ክቡር ዓላማዎች ከግባቸው ለማድረስ በፖለቲካ ድርጅት መልክ ተደራጅቶ ሕዝባዊ የለውጥ እንቅስቃሴን በሕዝቡ ውስጥ ለማድረግ በቅድሚያ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድነት ድርጅት (ኢሕአድ) በኋላም የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) የሚል ስያሜ ያገኘውን በሀገሪቱ ታሪክ የመጀመሪያውን ዘመናዊ የፖለቲካ ፓርቲ በሚያዚያ ወር 1964 ዓ.ም የመሠረተው።

ኢሕአፓ የተመሠረተው በወቅቱ አገሪቱ የነበረችበት ነባራዊ ሁኔታ መሠረታዊ ለውጥን ግድ በማለቱና ይህን ትግል ሊመራ የሚችል ዘመናዊ የፖለቲካ ፓርቲ መመሥረት አስፈላጊ ግዴታ በመሆኑ ነበር። የፓርቲው መሥራቾች ፓርቲውን የመሠረቱት ፓርቲ ያስፈልገናል በሚል ግልብ ስሜት ተነሳስተው ሳይሆን በኢትዮጵያ ለውጥን ጠያቂ የሆነ "አብዮታዊ ሁኔታ" መኖሩንና ይህንንም የሚመራ ተራማጅ የፖለቲካ ፓርቲ አስፈላጊ መሆኑን አስቀድመው በመረዳታቸውና በማየታቸውም ነበር። በየካቲት 1966 ሕዝባዊ አብዮት ይከሰታል የሚል ትንቢት ባይኖርም የፓርቲው መሥራቾች እየጨመረ የነበረውን የሕዝብ ብሶትና ባጠቃላይም የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ በተገቢው መንገድ ተገንዝበው መጭው ሁኔታ ምንን ጠያቂ ሊሆን እንደሚችል አስቀድመው ማየት የቻሉ ነበሩ። በሌላኛው በኩል ደግሞ፣ በኢትዮጵያ አብዮታዊ ሁኔታም ሆነ የተባለውን ፓርቲ ለመመሥረት የሚያበቃ ሁኔታ የለም ያሉና በኋላ ደርግን የተቀላቀሉት ክፍሎችም ሁኔታዎችን በተገቢ መመርመር የተሳናቸው ከዛን ጊዜ ጀምሮ ነበር ለማለት ይቻላል።

ፓርቲው ተመሥርቶ እንቅስቃሴ የጀመረበት ወቅት ሰዩመ መለኮትነትን መለያው ያደረገውና ከ40 ዓመት በላይ የቆየው የዘውድ አገዛዝ ገበሬውን በጭሰኝነት፣ ከፍተኛ ግብር በመጫንና በጉቦ (በሙስና) በዘቀጠ የፍርድ ሥርዓት ተብትቦ የያዘበት፤ ሠራተኛው በውጭ ኩባንያዎች ለአስከፊ ብዝበዛና ዘረኝነት የተጋለጠበት፤ "ሴክተር ሪቪው" የተባለውን ትውልድ ገዳይ የትምህርት ፖሊሲ በሥራ ላይ እንዲውል የታቀደበት፤ ሕዝብ በኑሮ ውድነት የሚሰቃይበት፤ በርካታ ዜጎች በረሀብ የሚረግፉበት፤ ብሔረተኛ እንቅስቃሴዎች ብቅ ብቅ ያሉበት፤ ... ወዘተ ሁኔታ ሲሆን በሌላ በኩል፤ ደግሞ የዘውዱን አገዛዝ በመቃወም አርሶ አደሩና ሠራተኛው በተለይም የተማረው ክፍል አልገዛም ብሎ የተነሳበትና "መሬት ላራሹ"፣ "የድሃው ልጅ ይማር"፣ "ለሠራተኛው የደሞዝ ጭማሪ"፣ "ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም" ብሎ ድምጹን ያሰማበት፤ የአዲስ ሥርዓትና አስተዳደር ፍላጎት የአሮጌውን ሽረት የጠየቀበትና አገራችን የካቲትን ያረገዘችበት ወቅት ነበር።

በ1966 በየካቲት ወር በኢትዮጵያ ውስጥ የተጀመረው ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል የተሳተፈበት የሥርዓት ለውጥ እንቅስቃሴ በመላ የሀገሪቱ ክፍል ሲፈነዳ ኢሕአፓ እንደ ፖለቲካ ድርጅት ከተመሠረተ ገና ሁለት ዓመቱ ነበር። በወቅቱ የአብዮቱ ሁኔታ ግን በመላው የሀገሪቱ ክፍል እንደ ሰደድ እሳት የተቀጣጠለው የለውጥ እንቅስቃሴ ኢሕአፓን ከሞላ ጎደል በመላ የሀገሪቱ ከተሞች ቶሎ እንዲደራጅና እንዲጠናከር ረድቶታል።

የኢሕአፓ ልሳን የሆነችው ዴሞክራሲያም በወቅቱ የኢሕአፓ ልሳን መሆንዋ ሳይገለጽ እሰከ ነሐሴ 1967 ዓ.ም ማለትም እስከ ፓርቲው እወጃ ነሐሴ 26 ቀን 1967 ዓ.ም ድረስ ባለማቋረጥ በተከታታይ እንድትወጣ ተደርጓል። ዴሞክራሲያ አንቂ ብቻ ሳትሆን አደራጅም በመሆን አገልግላለች። ዛሬም ይህንኑ ሚናዋን ሳታቋርጥ ቀጥላለች። ዴሞ በሀገሪቱ ውስጥ የሚታዩትን ዓብይ ፖለቲካዊ፣ ኤኮኖሚያው፣ ማኅበራዊ፣ ...ወዘተ ጥያቄዎችን እያነሳች "የት ደርሰናል?"፤ "ምንስ ይጠበቅብናል?" በሚሉና የአገራችንን መጻይ ሁኔታዎችን በመዳሰስ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከአምባገነኖች ጭቆና ለመላቀቅ የሚያደርገውን ትግል አቅጣጫ በመጠቆም የበኩሏን ታሪካዊ ኃላፊነት ለመወጣት የምትሞክር የድርጅቱ ልሳን ነች። ራሱን ደርግ በሚል የሰየመውን ወታደራዊ አምባገነን አገዛዝ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ገጽታዎች በማሳየት አምባገነናዊና ፋሽስታዊ ባህርያት እንዳሉት በመግለጽ ሕዝቡ ያነሳቸውን የመሬት ላራሹ፤ የዴሞክራሲና የሕዝባዊ መንግሥት ጥያቄዎችን

በማብራራትና የትግል አቅጣጫን ሳታቋርጥ በመጠቆም ከፍተኛ ሚናን ተጫውታለች። ይህንኑ ታሪካዊ ሚናን ዛሬም በቀጣይነት እየተወጣች ትገኛለች።

የኢሕአፓ መለያ ከሆኑ ጎላ ብለው የሚታወቁ እሴቶቹ መካከል በሕዝብ ተወዳጅነቱ፣ ድርጅታዊ ነጻነቱ፣ መጭ ሁኔታዎችን አስቀድሞ በማየቱ፣ በሕዝብና በአገሩ ሉዓላዊነት የማይደራደር ወይም አይበገሬነቱን፣ ...ወዘተ ማንሳት ይቻላል።

- በኢትዮጵያ አብዮት ሊከሰት እንደሚችል ቀደም ብሎ ማየቱ
- የየካቲት አብዮት በጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ካልተተካ የተደራጀው ኃይል የወታደሩ ክፍል የሕዝቡን ሥልጣን ሊነጥቅ እንደሚችል በአጽንዖት ማሳሰቡ፤
- ራሱን ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ በሚል ሥልጣን የያዘው ወታደራዊ አገዛዝ ያራመደው የኢትዮጵያ ትቅደም ያለምንም ደም የሚለው መፈክር ሕዝቡን ማዘናጊያ ከመሆን እንደማያልፍ፣ ሥልጣኑን በፈቃዱ እንደማይለቅና እንዲያውም ሀገሪቱ በፍጹማዊ የፈላጭ ቆራጭ (ፋሽስታዊ አገዛዝ) መዳፍ ሥር ልትወድቅ እንደምትችል አስቀድሞ ማስጠንቀቁ፤
- ወታደራዊው አገዛዝ ባለቀለትም ጊዜ ህወሓት በሚል ስም የሚንቀሳቀሰው የወያኔ ቡድን ስልቱን ቀይሮ ኢትዮጵያዊ ነኝ በሚል ወደ ሥልጣን ከመጣ አገሪቱን በዘር ከፋፍሎ ልትወጣው ወደማትችለው ቀውስ ሊከታት የሚችል ፀረ-ኢትዮጵያ፥ ጠባብ ብሔረተኛ ቡድን መሆኑን አሳውቆ አገር ወዳድ ኃይሎች ሁሉ ይህን ለመከላከል በአንድነት መቆም እንዳለባቸው ማስጠንቀቁ የሚጠቀሱ ናቸው፤

ለኢትዮጵያ ህላዌ፣ ለሀቀኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ያለውን በጎ ፍላጎትና ለዚህና ለሀገርም ሲባል ሊከፈል የሚገባ መስዋዕትነት ካለ በጊዜውና በቦታው በተግባር ለመክፈል ያለውን ዝግጁነት ገላጭም ሆኖ እናገኘዋለን።

እነሆ ባሁኑም ጊዜ፤ ኢትዮጵያዊነትን እንደ ታክቲክ አስተጋብቶ ሕዝብን በማዘናጋት የወያኔን ዘረኛ ሥርዓት ለማዳን ወደ ሥልጣን የመጣው አዲሱ ሹም አፄ ምኒልክ ቤተመንግሥት ከመሰየሙ አስቀድሞ ግለሰቡ የነበረውን ወያኔያዊ ሥርዓት እድሜ ለማራዘም በባዕዳን እንደታጨልን ማጋለጡና ሕዝብ ሳይዘናጋ ትግሉን ቀጥሎ የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም አበክሮ መምከሩ የፓርቲውን አስቀድሞ የማየት ባህርይ አመላካች መሆኑን መጥቀሱ አስፈላጊ ይመስለናል።

እነዚህ አይነተኛ የድርጅቱ ባህሪያት በኢሕአፓ ዙሪያ ለተሰባሰቡና ባጠቃላይ ለወገንና ለሀገር ኩራት ቢሆኑም በዚያው ልክ ደግሞ፣ የአገር ውስጥ እበላ ባይ ክፍሎችና (በተለይ አድርባይ ምሁራን) አምባገነን አገዛዞች በአንድ በኩል ፤ እነዚህን ፀረ-ሕዝብ ክፍሎች በመጠቀም ጥቅማቸውን የሚያጋብሱ ባዕዳን ኃይላት በሌላ በኩል አስጊ ነው የሚሉትን ድርጅት ላለፉት 47 ዓመታት ለማፍረስ ያልሸረቡት ሴራ ያላጠመዱት ወጥመድ አልነበረም። ኢትዮጵያን ለማፍረስና የሕዝቡን አንድነት ለማዳከም በተለይም አዲሱ ወጣት ትውልድ የኢሕአፓን እውነተኛ ታሪክ እንዳይረዳ ለማድረግ በበሬ ወለደና በጥቁር ወተት ትንግርት ጭምር ኢሕአፓ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ያለውን ተቀባይነት ለማሳጣት ያላሰማሩት ጥላቻ ሰባኪ፣ የሀሰት ክስ ደርዳሪ፣ የብዕር ተቀጣሪ፣ የአንጃ አጫፋሪ፣ ምሁር ነኝ ባይ መሠሪ የለም ማለት ይቻላል። እነዚህ የአገርና የሕዝብ ጠላቶች ያልተረዱት ነገር ቢኖር ኢሕአፓ ማለት እስራትና ሞት ስደትና ግርፋት፣ ጊዜና ፈተና የማይነቀንቀው የዓላማ ፅናትን ስጋ ወደሙ ያደርገ የሕዝብ ወገን መሆኑን ነው። የኢሕአፓን አገር ወዳድነትና ሕዝብ አክባሪነት ለሚጠይቁና ለሚያጥላሉ ክፍሎች የአለን መልስ ዛሬም እንደትናትናው ያማሻማ ግልጽ የሆነ ነው። የአገር ሉዓላዊነት ሲደፈር፤ ፍትህ ሲዛባ አምባገነኖች በሕዝብ ጫንቃ ላይ ሲፈራርቁ የት ነበራችሁ? ሚናችሁስ ከነማን ጋር ነበር? ነው መልሳችን።

ኢሕአፓ ቆራጥና ጀግና ታጋዮችን በማሰበሰብ ለሕዝብም ሆነ ለሀገር ክብርና ጥቅም የቆመና የታገለ ድርጅት በመሆኑ የሕዝብ ወገኖች የሆኑ ይሳሱለታል ይንከባከቡታል። በአንፃሩም ጸረ-ሕዝብና ጸረ-ኢትዮጵያ የሆኑ ክፍሎች ሁሉ ሊያዳክሙትና ሊያጠፉት ተከታታይ ጥረቶችን ሲያደርጉ ቆይተዋል። እነዚህ የውስጥና የውጭ የሕዝብ ጠላቶች ኢሕአፓን ጨርሶ ለማጥፋት ባይቻላቸውም፣ ለማዳከም እስከዛሬ ባላባራው ዘመቻቸው ያልፈነቀሉት ድንጋይ ያልቆፈሩት ጉድጓድ አለ ለማለት አይቻልም። በኢሕአፓ ላይ አሰከዛሬ የዘመቱትን ክፍሎች ማንነት በጥልቀት ስንመረምር ሁሉም ለአቋማቸው በቂ ምክንያቶች እንዳሉዋቸው እንገነዘባለን። ባዕዳን ኃይላት በተለይም ምዕራባውያንና አረቦቹ ኢሕአፓ የኢትዮጵያ ነፃነትና ሉዓላዊነት ይከበር በማለቱና በጥቅም የማይገዛ በመሆኑ፤ የኢትዮጵያን ድንበር የደፈሩትን (ሱዳን፣ ሱማሊያ) ወዘተ... በጽናት በመቃወሙ፤ በጠላትነት ፈርጀው በየፊናቸው አጥቅተውታል።

ኢሕአፓ በኢትዮጵያ ሀገራዊ ሉዓላዊነት ይከበር በማለቱ፣ በእኩልነት ላይ ለተመሠረተ የአገር አንድነት አቋም በመያዙና ጠባብ ብሔርተኞች ሀገር ለመገነጣጠል በሕዝብ መሀል ጥላቻን ለመፍጠር የኢትዮጵያን ታሪክ በርዘው ህልውናዋን ለመሰረዝ ሲሞክሩ አይሆንም በማለቱ ከወያኔ እስከ ሻዕብያ ከኦነግ እስከ ምሶነግ (WSLF) በጠላትነት መድበው አብረው ወግተውታል፤ ታግለውታል፤ ሊያጠፉትም ጥረዋል።

የተለያዩ ዓላማ ያላቸው የድርጅቱ ጠላቶች ኢሕአፓን ከውስጥ ለመከፋፈልና ለማዳከም ከውስጡ የበቀሉ እንክርዳዶችን እንደመሣሪያ በመጠቀም ድርጅቱን ለማፍረስ ጥረት አድርገዋል። ዓላማችንን ቀይረን ቃል ኪዳናችንን አፍርሰን ፤ ለአምባገነኖች/ለጉልበተኞች እንደር በማለት በድርጅቱ ውስጥ አቋም ይዘው የተንቀሳቀሱትን ከሀዲ አንጃዎች አሻፈረኝ ስላላቸው ለጠላት ወዶ ገባ ሆነው ድርጅቱን አውግዘውታል። ከጠላትም ወግነው ዘምተውበታል።

ኢሕአፓ ትናትንም ሆነ ዛሬ የኢትዮጵያን ክብርና ሉዓላዊንትና የሕዝብን መብትና ጥቅም የሚደፍሩ የቅርብም ሆነ የሩቅ ጠላቶችን አምርሮ ይታገላል። ትናንት በሕዝብ ላይ ተፈናጠው ሲፏልሉ የነበሩትን የሥልጣን ጥመኞች ደሙን አፍስሶ እንደታገላቸው ሁሉ የዛሬዎቹንም ቅጥረኞችና አድርባዮች አምርሮ ይታገላል። የኢሕአፓን ህልውና ግድ የሚያደርገው የሀገርና የሕዝብ ብሶት ነው። የኢሕአፓ ዓላማና መሠረቱ የሕዝብ መብትና ጥቅም ብቻ ነው። ኢትዮጵያ ከነሕዝቧ ሳትከበርና ሳትታፈር ኢሕአፓ ትግሉን መቼም ቢሆን መቼ አያቋርጥም። የኢሕአፓን ስም ቀምቶ ለዘረኞች/ለወኔ በባለሟልነት በማደር ኢሕአፓን ለማርከስ የሚደረጉ ጥረቶች ከንቱ ሆነው ይቀራሉ። ኢሕአፓ ላይጠፋ አምባገነን ዘረኞችን ወያኔዎችን በከንቱ አትልፉ ስንል፤ አድርባይ ከፋፍዮችንም አትልከስከሱ የሀቀኛ ታጋዮችን ገድል፤ ባጠቃላይ ሀገርን በከንቱ አታርክሱ የምንለው ለዚህ ነው።

የኢትዮጵያን አዲስ ዓመት መባቻ ወርሀ መሰከረምን ስናከበር ሁሌም የምንዘክረው ኢሕአፓ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሰንቆ የተነሳውን ብሩህ ተስፋና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብሥራት የሆነውን የድርጅቱን ራዕይ በአደባባይ ያበሰረበት በመሆኑ ጭምር ነው። ኢሕአፓ ሲመሰረት ቋንቋ ሃይማኖትና ፆታን ሳይለዩ በኢትዮጵያዊነት የተሰባሰቡት የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች፤ ጭቆና ብዝበዛና የግፍ አገዛዝን ከሚወዷት አገራቸው አስወግደው ፍትህ ርትዕ የሰፈነባት፤ ሁሉም ዜጋ በእኩልነት የሚኖርባት ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ነበር የዛሬ 45 ዓመት (1967-2012) በወርሃ መስከረም መጥቢያ (ነሐሴ 26 1967) እራሱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያስተዋወቀው/ይፋ የወጣው። እነሆ ከተመሠረተ አርባ ሰባት(47) ዓመት። ይፋ ከወጣ ደግሞ አርባ አምስት(45) ዓመት የሞላው የእድሜ ባለጸጋና የትግል ተመክሮን ያካበተው ኢሕአፓ ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥቅምና አገራዊ ህላዌ የተፈታተኑ አገዛዞችን ለአፍታም ሳያመነታ የታገለ፤ ዛሬም ለኢትዮጵያ ሕዝብ የገባውን የትግል ቃል ኪዳኑን ሳያጥፍ መክፈል የሚገባውን መስዋዕትነት እየከፈለ በጽናት ትግሉን የቀጠለ ኢትዮጵያዊ ድርጅት ነው።

አሮጌው ዓመት አልቆ አዲሱ ሲተካ፤ ዛሬም የኢትዮጵያ ሕዝብ በደሙ በዋጀው መስዋዕትነት የሚገባውን ክብርና ጸጋ አለመጎናጸፉ ብቻ ሳይሆን ፤ የነበረው ምኞትና ተስፋ፤ ያደረገው የዘመናት ትግል ጨኸቱን በቀሙ በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ሥም በሚምሉና በሚነግዱ ዘረኛ ሸቃጮችና የባዕድ ቅጥረኞች ብሔራዊ ክብሩ ተደፍሮ የሥልጣን ባለቤትነቱን ተነጥቆ ፤ ራሱን በራሱ ለማስተዳደር የነበረው የፍትሕ ጥማቱ ተጨናግፎ ሀገሪቱ የዋይታና የሰቆቃ፤ የልቅሶና የጽንፈኞች መቦረቂያ በሆነበት ሁኔታ ውስጥ መገኘታችን ነው። በወርሀ መሰከረም በአዲሱ ዓመት ዛሬም እንደ አዲስ ፤ ለአፍታ ቆም ብለን ራሳችንን መጠየቅ ያለብን ቁምነገር እንዳለ እንረዳልን። ለመሆኑ ይህ ዘረኛ፤ ከፋፋይና ጸረ-አንድነት ኃይል (ወያኔ) እንዴት ኢትዮጵያን ለማዳከምና ለማፍረስ አደጋ ሆኖ ሊከሰት ቻለ? የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ ነው። ወያኔ ለሥልጣን የበቃው በአንድ በኩል ፋሽስቱ መንግሥት (ደርግ) ባደረሰው እልቂትና ወታደራዊ ጡንቻውን በተገንጣዮች ላይ ሳይሆን እስከ ዕድሜ ማብቂያው ወታደራዊ ክንዱን ዴሞክራሲያዊ መንግሥት በጠየቁት ክፍሎች ላይ በማሳረፉ፣ ጦሩን በካድሬዎቹ ቁጥጥር ሥር ማድረጉና አሉ የተባሉ ጀኔራሎችን መግደሉ መሆኑን ይጠቅሷል። በዚህም የወታደሩ ሞራል በመዳከሙና ከአንድነት ኃይላት ጋር ህብረት መፍጥር እንደነበረበት ለመረዳት ቅንነቱን ማጣቱ፤ ... ወዘተ የመሳሰሉትን ከብዙ በጥቂቱ ማንሳት ይቻላል። በሌላ በኩል ደግሞ ሀገር ወዳዱ ዜጋ ለደርግ በነበረው ጥላቻ ተዘናግቶ፤ በውዥንብር ተጠምዶ ለወያኔ ሰለባ በመዳረጉ መሆኑ የሚካድ አይደለም።

ዛሬም ለውጥ የለም ስንል ያለፈው እንዳይደገም ማለታችን ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ “ተቀመጥ በወንበሬ ተናገር በከንፈሬ” ብሎ የሰየመው የራሱ የሆነ ሕዝባዊ መንግሥት አልመሠረተም፤ የሥልጣኑ ባለቤት አልሆነም ማለታችን ነው። ዛሬም ጸጥታው፥ ጦሩና ቢሮክራሲው፥ ... ወዘተ ሙሉ በሙሉ በአገዛዙ ቁጥጥር ሥር ናቸው። ዛሬም አገራችን በሺዎች የሚቆጠሩ የፖለቲካና የህሊና እስረኞች ማጎሪያነቷ እንደቀጠለ ነው።ዛሬም ቁልፍ ቁልፍ የሆኑ የመግሥት ተቋማት ከወያኔ ቁጥጥር ወደ ኦህዴድ/አዴፓ ተዛውረዋል። ዛሬም በነጻ ፕረስ ሥም ጽንፍኞች (ተረኞቹ) ተደራጅተው ሀሰትና ውዥንብር ቂም በቀልና ጥላቻን በሕዝብ መሀል ይነዛሉ። ሀቀኛ ዘጋቢዎችና የሕዝብ ወገን ጋዜጠኞች ይዋከባሉ። ዛሬም ጭፍን የተረኝነት አድሎ መረኑን ለቋል።

በነጻ ገበያ ኤኮኖሚ ሥም የሀገሪቱን ዋና ዋና ብሔራዊ የልማት ድርጅቶችን ሙሉ በሙሉ ወይንም በከፊል ለመሸጥ አዲሱ ሹም የጌቶቹን (የዓለም የገንዘብ ድርጅት፥ የዓለም ባንክን) ጥቅምና ፍላጎት ለማስጠበቅ የሚወስደው የተሳሳተ የኤኮኖሚ ውሳኔ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና አገራዊ ጥቅም አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ነው። ሕዝባዊ ተቋማት በሌሉበትና በሕዝብ ተመርጦ ሕዝባዊ ቁጥጥር የሚደረግበት መንግሥት ባልተመሠረተበት ፤ አገዛዙ ከእግር ጥፍሩ እስከ ራስ ጸጉሩ በጎጥ በተተበተበበትና በሙስና በተዘፈቀበት ሁኔታ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንጡራ ሀብት የሆኑትን እንደ አየር መንገድ ፤ የኢትዮጵያ

ቴሌኮሙንኬሽንና የኢትዮጵያን ምድር ባቡር፣ ... ወዘተ የመሳሰሉትን ለሽያጭ ማቅረብ አገርን ከማፍረስና በርካታ ዜጎችን ከሥራ ገበታቸው አላቆ ለሥራ አጥነት ከመዳረግ ባለፈ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሞት ለባእዳኑ ደግሞ ሠርግና ምላሽ ነው። የእነሱ/የአምባገነኖች ጥቅምና ፍላጎት ሕዝብ ከሚለው፣ ከሚፈልገው ጋር ጨርሶ አልገጥም እያለ፤ በገሀድ እየተቃረነ ሀገር እየፈረሰች ባለችበት ሁኔታ፤ ከፊት ለፊታችን የተጋረጠውን ድቅድቅ ጨለማ ብርሃን ነው በማለት የተለመደውን የአፓርታይድ የአገዛዝ ሥልጣናቸውን ለማስቀጠል ደፋ ቀና ሲሉ ይታያል። ለዚሁ አኩይ ድርጊታቸው የምዕራቡም ሆነ የአረቦች ድጋፍ አልተለያቸውም።

የዛሬዎቹ ገዥዎች (ሹሞች) የሕዝብን መፈክር ቀምተው አፍጦና አግጦ የቀጠለውን ኢ-ዴሞክራሲያዊ አገዛዛቸውን የቃል ቅባ ቅዱስ እየቀቡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ሥም እየማሉና እየተገዘቱ እያወናበዱ አንዳሉ ለማየት አያዳግትም። እቅጩንም ለማወቅ ሩቅ ሳንሄድ የትናንቱን የራሳችንን የአምባገነኖቹን ታሪክ በበቂ የሚያስተምረን ስለሆነ ከሚነገረውና እየተፈፀመ ካለው በስተጀርባ መጋረጃውን ገልጠን የሹሙን ተግባርና ትክክለኛ ዓላማውን፤ መመርመርና ማወቅ ይጠበቃል ብሎ ኢሕአፓ በፅኑ ያምናል።

ከውጭና ከውስጥ የተሰባሰቡት ጽንፈኞች ፤ ዓለም የመሰከረውን ታሪክ የመዘገበውን ሐቅ፤ ደልዘውና አርክሰው "ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የፈጠራ ወሬ ነው" በሚል ሊፍቁና የራሳቸውን የፈጠራ ታሪክ እንደ አኖሌው ሊያቆሙ፤ አዲስ መልክዓ-ምድር (ካርታ) በመሳል ከአረቦቹና ከምዕራባውያኑ በተቸራቸው ዲናርና ዶላር ኢትዮጵያን እንደቅርጫ ሥጋ ቆራርጠው ሊከፋፍሏት አሰፍስፈዋል። ለብሔረሰቦች ጥያቄ መፍትሔው ልዩነትን ማራገብ፤ ድንበር ማካለልና አገር መሸንሸን ሳይሆን እኩልነትን አረጋግጦ በዚሁ መሠረት አንድነትን ማዳበር ሆኖ ሳለ ወያኔና ወያኔ የቀፈቀፋቸው ጽንፈኖች መገንጠልን በማንገስ፣ ክፍፍልን በማስቀደም አገርን ለማፍረስ እያደቡ ይገኛሉ። ኢትዮጵያን ለመካድ የጋራ ታሪክን ጉድጓድ ምሶ አፈር ማልበስ የጎጠኞች ዋና ተልእኮ ነው። ትናንት እነኢሳያስ አፈወርቅ "ኤርትራ የምትባል አገር ጥንትም ነበረች የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ሆነች፤ ለኢትዮጵያ ባዕድ ነች፤ ... ወዘተ" እያሉ የቀባጠሩት አለምክንያት አልነበረም። ከጽንፍኞቹ መንደር እየሰማነውና እያየነው ያለነው የፀረ ምኒልክ ዘመቻም የራሱ የሆነ ዓላማ አለው። ይህም እርኩስ ዓላማ፤ የጋራ ታሪክንና ኢትዮጵያን ለመካድና ለማፍረስ የሚደረግ ዘመቻ አካል ነው። በኢትዮጵያዊነታቸው አምነው ለኢትዮጵያ የተሰውትንና መከራ የተቀበሉትን የኦሮሞ ተወላጅ አርበኞች እንዳልነበሩ ተደርገው የሚቆጠሩት ወይም የሚወነጀሉት ለዚሁ አሳፋሪና አጸያፊ አገር የማፍረስ ዓላማ ነው።

የኢትዮጵያ ሕልውና ታሪክ የዘመቻ/የጦርነት ታሪክ ሆኖ የቆየው ብዙ ቋንቋዎች የሚነገሩባት፤ የበለጸገ የጥንታዊ ባህልና ሃይማኖቶች ባላጸጋ የሆነችን አገር አንድነት በማዳከም የራሳቸውን ለመጫን በከጀሉ የውስጥና የውጭ ኃይላት ጋር መዋደቅ ግዴታ ሆኖ ስለኖረ ጭምር ነው። አጼ ምኒልክ መላው ኢትዮጵያን በማስተባበር ታላቁን የአድዋ ድል በማስመዝገባቸው በፀረ-ኢምፔራሊስትና በፀረ-ቅኝ ግዛት ትግል ለኢትዮጵያዊያን ብቻ ሳይሆን ፤ ለሁሉም የነፃነት ተዋጊና በተለይም ለመላው ጥቁር ሕዝብ አንድ ታላቅ ገድል አስምዝገበዋል። ለዘመናዊነትም ታላላቅ መሠረቶችን ጥለዋል። ይህንን የጀግነንት ታሪክ እኛ ኢትዮጵያውያን ካላወደስነውና ካልዘከርነው ማን ሊያውድሰውና ሊዘክረው ይችላል?

አጼ ምኒልክ በዘመናቸው ኢትዮጵያ ወደ ሃያኛው ምዕተ ዓመት የሥልጣኔ ዘመን እንድትሸጋገር በፖለቲካው፣ በኤኮኖሚው በማኅበራዊውና በወታደራዊ፣ ...ወዘተ ፈርጆች ያደረጉትን የአገር ግንባታን ጥረት ሁሉ የዘመናችን ቅጥረኞችና ጽንፈኞች አርክሰውና ደምስሰው አጼ ሚኒልክን በወራሪነትና በቅኝ ገዥነት ሳይቀር መፈረጃቸው አገርን ለማፍረስ ታሪክን መሠረዝ የሚለውን የባንዳ መርሃ ግብርን ተከትለው ነው። ቅን ልቦናና አስተዋይ አዕምሮ ያለው ዜጋ የኢትዮጵያን አመሠራረት ታሪክ ጉዳይ ከስሜትና ከጥላቻ ባሻገር ከዓለም ታሪክና የኅበረተሰብ እድገት ሂደት እንዲሁም ከአገሮች አመሠራረት አንጻር ማየት አይሳነውም።

አድገዋል ሰልጥነዋል የሚባሉ የአውሮፓ አገሮችም ሆነ ሌሎች በዓለም ላይ ያሉ አገሮች ያለፉበትን ታሪክ መመርመርና መንገዱስ ምን ምን ነበር ብሎ መጠየቅና የእኛስ የተለየ ነውን? ብሎ ማገናዝብ ተገቢና አስፈላጊም ነው። አዎ ጥፋት ተሰርቷል ቢባልስ የአሁኑ ትውልድ ለያኔው ጥፋት ተጠያቂና እዳ መክፈል አለበት? ስለ አለፈው በማላዘን ሥልጣኔን ማግኘት እንደሚቻል አድርጎ፤ በዛሬ መነፅር ያለፉ ድርጊቶችን እየቆፈሩ ታሪክን ማጨለም የምንመኘውን ሰላም፣ ብልጽግናና አንድነት ለማግኘት የሚያስችለን መንገድ ሊሆን አይችልም። የሀገራችን ታሪክ መጻፍ ያለበት ቢሆንም ያልነበረን ድርጊት መደርደርና እውነተኛ ታሪኩን ሆን ብሎ ማፋለስ ዋጋ የሌለው ከመሆኑም በላይ ጎጅ ነው። ይልቅስ የሚያዋጣው ከትናንቱ ስህተት ተምሮ ለዛሬዎቹ ችግሮች መፍትሔ አሁን በደረስንበት መነጽር አሻግሮ በማየት ሚዛናዊ ግንዛቤን ማዳበር ነው።

እንደተለመደው በአሁኑ ወቅት በሥልጣን ላይ ያለው አገዛዝ "በሕዝብ የተመረጥኩ ነኝ" ብሎ ራሱን በራሱ ለመቀባትና ለማንገሥ ፤ ራሱ መርጦ ፤ ራሱ ሸልሞ በሾመው "የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ" አማካኝነት የተለመደውን የምርጫ ቧልት ይዞ ብቅ ብሏል። ይህ የኢትዮጵያን ሕዝብ እሬት እሬት ያሰኘ የተለመደ ወያኔያዊ የማጭበርበሪያ ተውኔት ለኢትዮጵያ ሕዝብ በአዲስ አመት አዲስ ምዕራፍ የሚከፍት ሳይሆን ቀጣይ የስቃይና የመከራ አገዛዝን የሚያራዝም፤ ሕዝቡን ለበለጠ ስቃይና

መከራ የሚዳርግ፤ ሀገራችንንም ለበለጠ አደጋ የሚጋብዝ ነው። እንደተለመደው የወያኔ ድራማ፤ ወያኔ ከራሱ ጋር (ጎጠኛ ከጎጠኛ) ተወዳድሮ በአሸናፊነት ወጥቶ፤ ያው ለ28 ዓመት አጅ እጅ ያለውን ጎጠኛ አገዛዝ በምርጫ ሥም አቆናጅቶና በታማኝ ተቃዋሚዎቹ አሳጅቦ፤ በፈጣሪዎቹ (በባእዳኑ) ቡራኬውን ተቀብሎ አገዛዙን ለማስቀጠል ነው።

ስለሆነም በቃኝ እምቢኝ ማለትን የረሳ ሕዝብ ሁሌም በጨቋኞች ይቀየዳልና በወያኔ ምርጫ ተገኝተን ለወያኔ የምርጫ ድራማ ተዋናይ አንሆንም ማለትና በምርጫው አለመሳተፍ፤ የሚካሄደው ምርጫ የዘረኞችና የአምባገነኖች ሽፍጥ መሆኑን ማሳየት፤ ሀገሩን ከሚወድና ባርነትን ከሚጸየፍ ዜጋ የሚጠበቅ ተግባር ነው። ከመለስና ከኃይለማሪያም ከአብዮት (ከአብይ)ና ከደብረጽዮን ከደመቀና ከመገርሳ መሃል ምረጡ መባል ምርጫ አለመሆኑን ፤ በገቢር ማሳየትና ቀልዱን አቁሙ ማለት ይገባል። አገርን ለማፍረስ ከተነሱ ጎጠኞች ጋር መተባበር አገርን የሚያፈርስ ሰነድ ላይ ፊርማን የማስቀመጥ ያህል ከባድ መሆኑንም ከልብ ያጤኗል! ወያኔ ተመረጠ አልተመረጠ የራሱ ጉዳይ ቢሆንም፣ ከራሱ ጋር ተወዳደሮ መመረጡ አይቀሬ ነውና የእሱን ቧልት ለራሱ ለወያኔ ትተንለት ልንታገለው ይገባል። አስቀድመን እንደተናገርነው ዛሬም እንደትናንትናው በሥልጣን ላይ ያለው ያው ራሱ ዘረኛው ወያኔ ነው - ሥልቻ ቀልቀሎ ቀልቀሎ ስልቻ። የወያኔ ባለሥልጣናት ከአዲስ አበባ ወደ ትውልድ መንደራቸው ወደ መቀሌ አድዋና ሽሬ ቦታ ቀየሩ እንጂ ራሳቸውም ሆነ በጉዳይ አስፈጻሚያዎቻቸው አማካኝነት ወያኔያዊ አጀንዳቸውን ማለትም ኢትዮጵያን የማተራመስ፤ የማዳከምና የመበተን ዘረኛ ተልዕኳቸውን ከመቸውም ጊዜ የበለጠ እያፋጠኑ/እያጧጧፉ ለመሆኑ ምስክር መቁጠር አይጠበቅብንም።

ኢሕአፓ እራሱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይፋ የወጣበትን አርባ ሰባተኛ (47ኛ) ዓመት ነሐሴ 26 2011-ን ሲዘከር በአዲስ ዓመት ብሩህ ተስፋን ሰንቆ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለሚወዳት እናት አገሩ ሲመሰረት የገባውን ቃል ኪዳን አድሶ ዛሬም እንደትናንትናው ዘረኛውን አምባገነን አገዛዝ ለማስወገድ የሚያደርገውን ሕዝባዊ ትግል በጽናት ለመቀጠል ቃል ይገባል።

የኢትዮጵያም ሥርየት ከባዕድ እንደማይገኝ አምነን ለሀገራችን እንታገል ሥንልም ለግል ጥቅምና ዝና የሚደረገውን፤ ለተገፋውና ለተበደለው ሕዝብ ፋይዳ የማይሰጠውን መወራጨት ሳይሆን በተግባር የሚደረገውን ትግል እንታገል ማለታችን ነው። ድርጅት ለትግል አብይ መሣሪያ ነው። አንድ ላይ ከቆምን ጠንካሮች ነን ከተበታተንን ግን እኛም ተዳክመን አገራችንንም ለበታኞች መንጋ አጋልጠን አገር አልባ አንዳንሆን እንጠንቀቅ! በሀገራችን ታሪክ እንደምናየው ሥልጣን የሚጨብጡት ኋይላት የትናንቶቹም ሆኑ የዛሪዎቹ ሕዝብን ተክተው "እኛ እናውቅልሃለን" ብለው ምለውና ተገዝተው በሕዝብ ሥም መግዛት የመረጡ በመሆናቸው መሠረታዊ የሆኑ የአዲስ ሥርዓት አዋላጅና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ መሠረት የሚጥሉ ተቋማትን - ሕዝብ መክሮ ያፀደቀው ሕገ -መንግሥት፣ ነፃና ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ፣ ነፃ የፍትህ ሥርዓት፣ ነፃ የመከላከያና የፖሊስ ኃይል፣ .. ያሉትን - ነፃ ምርጫን፣ በነፃነት መደራጀትን፣ የተለየ ሀሳብን በነፃ መግለጽንና መሠል መሠረታዊ መብቶችን አምባገነኖች እንደጦር ይፈሯቸዋል። ወደ ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሸጋገር የሚቻለው ሁሉን ባሳተፈ የሽግግር ሂደት በመሆኑ ይህንንም ሆነ የአገራችንን ዘላቂ ሰላምና እድገት ዕውን ለማድረግ አምባገነንኖችን ተደራጅተን እንታገላቸው።

ኢትዮጵያ በሐቀኛ ልጆቿ እኩልነትና አንድነቷ ተጠብቆ እንድትቆም፤ እንድትቀጥል ከተፈለገ ነገ የነፃነትና የመብት ጎህ ቀዶ እንዲንሰራፋ ከተመኘን የትንናትና ማጥ ውስጥ ገብተን መንቦጫረቅ አይኖርብንም። የዛሬውን አስከፊ ወያኔን መስለን፣ በወያኔ ዘረኝነት ላይ "የእኛንም" ዘረኝነት ወልደን፣ ጠበን ዘቅጠን ለመታገል መቃጣት አይገባንም። በሕዝባችን መከራ፣ ስቃይና መስዋዕትነት ስንቶቹ የኢትዮጵያ ጀግና ልጆች ደማቸውን አፍሰው ባስገኙት ተመክሮ ተገርተን፣ ተቃኝተንና ትምህርት ቀስመን፤ ካለፈው ፀጋ የሆነውን ይዘን ፤ ክፉውን አግልለን፤ በአዲስ ዓመት በአዲስ ተስፋ በአዲስ መሠረት በተሻለ መንገድ ነገን እውን ለማድረግ መጣር ይኖርብናል።

አሮጊው ዓመት ሄዶ አዲሱ ሲተካ፤ መስከረምም ሲጠባ ትግላችን ወያኔን በኦህዴድ/በአዴፓና ኦነግ ለመተካት ከሆነ በደም መቀለድ ይሆናል። ትግላችን በተሻለ ግንዛቤ፤ በፅኑ መሠረት ላይ ይቁም፤ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ በጀገኖች ልጆቿ ታፍራና ተከብራ ለዘላልም ትኑር !

በተባብረ ሕዝባዊ ትግል የኢትዮጵያ ትንሣዔ ዕውን ይሆናል!
እናቸንፋለን !!